# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተሃል?**

፩. እግዚአብሔር ስለሚያፈቅርህ ለሕወትህ አስደናቂ እቅድ ሰጥቶሃል?

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3:16

፪. ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክነያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3:23

፫. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14:6

፬. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1:12

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




"ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና ... ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም።"
(መኃ 8፡ 6-7)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**July 7, 2019** | **ሰኔ 30፣ 2011 ዓ.ም.**

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| ቃል ............. | ፓ/ር (ዶ/ር) አሳየኸኝ በርሔ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት
እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን
እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"
(ዮሐ. 3፡16)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## ኢየሱስ ይወዶታል!

ፍቅር ጥልቅ ነገር ነው። ፍቅር አያስገድድም ነገር ግን ብርቱ ገፊ ነው። ከያኒያን ዜማን ከግጥም አዋህደው፤ ቀለም በቡርሽ አጣቅሰው፤ ድርሰት ከምናብ አፍልቀውና ምስል ከድምጽ አቀናብረው ስለ ፍቅር ጥልቀት፣ ጥንካሬና ውበት ይቀኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስም የፍቅርን ኃይል ሲገልጽ "ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና ... ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም" ይላል። (መኃ 8፡ 6-7) እግዚአብሔርም ሰውን የወደደበት ፍቅር እጅግ ብርቱና ጥልቅ ነው። እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ሰውን ሁሉ ወዷል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ፍቅር "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" በማለት ይገልጸዋል (ዮሐ. 3፡16) ይህ ፍቅር እርሶንም የሚጠቀልል ነው። እግዚአብሔር እኛ በሕይወት እንኖር ዘንድ ሃጢያት የማያውቀውን አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለኛ በደል በመስቀል እንዲደቅና እንዲሞት በመፍቀድ ለእኛ ያለውን ወሰን የሌለውን ፍቅሩን አሳይቷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል የሞተው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የለየውን የኃጢያት ግድግዳ በሞቱ አፍርሶ ለሚያምን ሁሉ የሚሆን የደህንነትን መንገድ ለማበጀት ነው። እግዚአብሔር ሰውን በምሳሌው ፈጥሮ እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላት፣ ምድርንም እንዲገዛና እንዲያስተዳድር ባርኮት፣ ከእርሱም ጋር ሕብረትን እያደረገ በገነት እንዲኖር በክብር ስፍራ አስቀምጦት ነበር። ነገር ግን ሰው በዲያቢሎስ ተንኮል ተታሎ የፈጣሪውን ትዕዛዝ በመተላለፍ መንፈሳዊ ሞትን ሞተ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ኃጢያት ገባ። ከዚያም በኋላ የተከተለው የአዳም ትውልድ ሁሉ በኃጢያት ስር ወደቀ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል" ይለናል። (ሮሜ 3፡23) ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ኃጢአት በአዳም ምክንያት ወደ ዓለም ገባ። የኃጢያት ዋጋ ወይንም ውጤት ሞት ስለሆነ በኃጢአትም በኩል ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።

ጌታችን ኢየሱስ ከቅድስት ድንግል ማሪያም ተወልዶ በመስቀል ላይ የሞተው በኃጢያት ምክንያት የመጣብንን የሞት ፍዳ ለመክፈል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ኃጢያት ሁሉ ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመዋል፣ ስጋው ተቆርሶ፣ ደሙ ፈሶ ለአለም ሁሉ የሚሆን የደህንነት ቤዛ ሆኗል። በክርቶስም መስቀል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የለየው ኃጢያት፣ በኃጢያትም ምክንያት በሰው ላይ ነግሶ የነበረው ሞት ተነስቷል። እግዚአብሔር በባህሪው ፍጹም ጻዲቅ ፍጹምም መሃሪ በመሆኑ የክርስቶስ ሞት የኃጢያትን ቅጣት በመክፈል የእግዚአብሔርን ጽድቅ ፈጸመ። የክርስቶስ ትንሳዔ ደግሞ የእግዚአብሔርን ምህረትና የማዳን ኃይል በመግለጽ ሙታን ለነበርን ለኛ የድነት መንገድ ሆነ። ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን በሞቱና በትንሳኤው ስንተባበር ለኃጢያት ሞተን ለጽድቅ ህያዋን እንሆናለን።